# የዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባ፡ የቤተሰብ/አሳዳጊ አጠቃላይ እይታ

የተማሪ ስም፡-                                                    ቀን፡-

**የዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባ ምንድነው?**

ትምህርት ቤቶች የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አሁንም ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆናቸውን ለማየት ቢያንስ በየሶስት ዓመቱ አንድ ጊዜ እንደገና መገምገም አለባቸው። ይህ ከመሆኑ በፊት፣ ያሉትን ውሂብ እና መረጃዎች ለመገምገም እና አዳዲስ ምዘናዎች ያስፈልጉ እንደሆነ ለመወሰን የዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባ ይካሄዳል። ይህ ስብሰባ ወላጆች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች አንድ ላይ በመሆን ወቅታዊ መረጃን ለመመልከት፣ ስጋቶችን ለመወያየት እና ቀጣይ እርምጃዎችን ለማቀድ የሚሰባሰቡበት ጊዜ ነው። አዳዲስ ግምገማዎች ካስፈለጉ፣ ትምህርት ቤቱ ግምገማው ከመጀመራቸው በፊት የወላጅ ፈቃድ ይጠይቃል።

በIEP ቡድን ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው - ወላጆችን ጨምሮ - ከጠየቀ ይህ ስብሰባ ከሶስት ዓመታት ባነሰ ጊዜ በተደጋጋሚ ሊካሄድ ይችላል። ቶሎ ለመገናኘት ምክንያቶች አዲስ መረጃን ወይም ሪፖርቶችን መገምገም እና/ወይም ስለ ተማሪው ወቅታዊ የትምህርት ፍላጎቶች የበለጠ መማርን ሊያካትቱ ይችላሉ።

**በአብዛኛው ጊዜ በዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባ ላይ የሚሳተፈው ማነው?**
- እርስዎ (ወላጅ ወይም አሳዳጊ)
- የልጅዎ አስተማሪዎች (አጠቃላይ እና ልዩ ትምህርት)
- የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም ረዳት ርእሰ መምህር (ወይንም የወከሉት ሰው)
- ልጅዎ ተዛማጅ አገልግሎት የሚያገኙ ከሆነ የዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች (እንደ ንግግር ወይም የኦኪፔሽናል ቴራፒስቶች)
- የትምህርት ቤት የስነ ልቦና ባለሙያ
- የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ
- የተማሪ ድጋፍ አስተባባሪ (SSC)
- ልጅዎ፣ ተገቢ ሲሆን
- በእርስዎ ወይም በትምህርት ቤቱ የተጋበዘ ሌላ ሰው

**ስለ ምን እንወያያለን?**
እርስዎን ጨምሮ ቡድኑ የሚከተሉት ላይ እና ተጨማሪ ፈተና አስፈላጊ መሆኑን ለመወሰን፣ የክፍል አፈጻጸምን፣ ደረጃውን የጠበቀ የፈተና ውጤቶች፣ የመምህራን ዘገባዎች፣ የተዛማጅ አገልግሎት ሰጪ ማስታወሻዎች  ከዚህ ቀደም የተደረጉ ግምገማዎችን ይገመግማል፡-
  - ልጅዎ አሁንም ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን
  - የልጅዎ ወቅታዊ የትምህርት ፍላጎቶች ምንድ ናቸው
  - ልጅዎ በአካዳሚክ እና በእድገት ላይ እንዴት እየሄደ ነው።

ብቁነትን ለመወሰን እና አገልግሎቶችን ለመምራት ያለው መረጃ ቡድኑ በቂ መሆኑን ከወሰነ እና እርስዎ ከተስማሙ፣ ያለ አዲስ ፈተናዎች ዳግመ ግምገማውን ሊጨርሱ ይችላሉ።

**የሚወሰነው ምንድነው?**
አንድ ላይ ቡድኑ የሚከተለውን ይወስናል፡-
- ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆንን ለመወሰን አዳዲስ ፈተናዎች ወይም መረጃዎች አስፈላጊ ከሆኑ
- ቡድኑ ብቁነትን ለማገናዘብ በቂ ውሂብ/መረጃ እንዳለ ከወሰነ፣ ቡድኑ በስብሰባው ወቅት የብቁነት ውሳኔ ላይ ሊደርስ ይችላል። የልጅዎን የብቁነት ምደባ ለመለወጥ እና/ወይም ልጅዎን ከልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ለማስወጣት የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል።

## በዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባው ወቅት እንደ ወላጅ/አሳዳጊ ያለኝ ሚና ምንድን ነው?

- የተዘመኑ ፈተናዎች ያስፈልጋሉ ብለው የሚያስቡ ከሆነ ይግለጹ።
- በስብሰባው ወቅት ውይይቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያድርጉ። ማስታወሻ፡ ለመሳተፍ የቋንቋ ትርጉም እና/ወይም የADA መስተንግዶ ከፈለጉ ትምህርት ቤቱን ያሳውቁ።
- ሃሳቦችዎን፣ አመለካከቶችዎን እና የሚኖሮዎትን ማንኛውንም ስጋት ለማካፈል አያመንቱ።
- እንደየ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያ ይጠይቁ።
- ለሚመከሩት አዲስ ግምገማዎች ፍቃደኛ መሆንዎን ወይም አለመሆንዎን ይወስኑ።

ማስታወሻ፡ ትምህርት ቤቱ የዳግመ ግምገማ ምዘናዎችን እንዲያካሂድ የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልገዋል። ነገር ግን፣ ትምህርት ቤቱ የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ እርምጃዎችን ከወሰደ እና እርስዎ ምላሽ ካልሰጡ ፣ ትምህርት ቤቱ ምዘናዎቹን ሊያካሂድ ይችላል።

## ለዳግመ ግምገማ እቅድ ማውጣት ስብሰባ መዘጋጀት

የበለጠ ዝግጁነት እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማዎት የሚከተሉት ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፦

- ☑ የቅርብ ጊዜ የሪፖርት ካርዶችን፣ የIEP ሂደት ማስታወሻዎችን እና ያሉትን የምዘና መረጃዎችን እና ሪፖርቶችን ይገምግሙ እና ያደራጁ። የIEP ሂደት ማሻሻያ እና የሪፖርት ካርዶች በ*ParentVue* ውስጥ ይገኛሉ።
- ☑ ቡድኑ ግምት ውስጥ ሊያስገብዋቸው የሚፈልጓቸውን ማናቸውንም የግል ሪፖርቶች ወይም ግምገማዎች ከስብሰባው በፊት ያቅርቡ።
- ☑ የልጅዎን ብቁነት ወይም የትምህርት ፍላጎት ለመወሰን ተጨማሪ ፈተና ያስፈልገዋል ወይ ብለው ያስቡበት። ምዘናዎች ያስፈልጋሉ ብለው ካመኑ፣ የትኞቹን እንደሆኑ ይመዝገቡ እና ሃሳብዎን ለቡድኑ ያካፍሉ።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች "የመነጋገሪያ ነጥቦች" የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች "ጥያቄዎች" የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ አንድን ሰው (እንደ ጓደኛ፣ ጠበቃ ወይም የቤተሰብ አባል) ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው ለማምጣት ካሰቡ ቦታ እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲችል ትምህርት ቤትዎ አስቀድመው ያሳውቁ።
- ☑ ለስብሰባዎ ለመዘጋጀት እርዳታ ከፈለጉ የወላጅ መረጃ ማእከልን በ703.228.7239 ወይም prc@apsva.us ያግኙ።

| ሊታሰብባቸው የሚገባ ጥያቄዎች | የመነጋገሪያ ነጥቦች/ተጨማሪ ጥያቄዎች |
|---|---|
| • የዚህ ስብሰባ ውጤቶች ሊሆኑ የሚችሉ ምንድናቸው?<br>• ቡድናችን ብቁነትን እንዲወስን የሚረዳው ምን መረጃ አለ?<br>• ቡድኑ አዳዲስ ግምገማዎች እንደሚያስፈልጉ ከወሰነ፣ አዲሶቹ ግምገማዎች ምን ይለካሉ?<br>• ዛሬ የምናደርጋቸው ውሳኔዎች የልጄን የ*IEP* ድጋፍ/አገልግሎቶች ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ? | |

LEARN MORE

እርስዎ ለመርዳት PRC እዚህ ይገኛል። 703.228.7239 ላይ ይደውልሉን ወይም prc@apsva.us ኢሜል ይላኩልን።

PEATC:- ጠቃሚ የወላጅ መብቶች

PEATC:- ምዘናዎችን መረዳት

VDOE: የዳግመ ግምገማ ቪድዮ

PEATC: ዳግመ ግምገማ

የVDOE የልዩ ትምህርት የቤተብ መመሪያ